የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)


## መጋቢት 1987 — መጋቢት 2003

## ኢፖእአኮ: ሰብአዊ መብት እንዲጠበቅ ስላደረገው የ16 ዓመት ትግል

ኢፖእአኮ የዛሬ 16 ዓመት በፊት የተቋቋመው የፖለቲካ እስረኞችን፣ በተለይም ባልታወቀ ምክንያት በሌሎች የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ተቋማት ጉዳያቸው ቸል የተባሉትን ሰቆቃ ለዓለም ማህበረሰብ ለማሳወቅ ነው። ላለፉት 16 ዓመታትም ዓላማዎቹን ለማሳካት ጥሯል፣ ስኬትም አስመዝግቧል።

ኢፖእአኮ የሰብአዊ መብት በኢትዮጵያ እንዲከበር በሚያደርገው ትግልም በመቶዎች የሚቆጠሩ መግለጫዎች አውጥቷል። በተለያዩ ብሄረሰቦችና የሃይማኖት ተከታዮች ላይ የተፈፀሙ የመብት ጥሰቶችን አጋልጧል፣ መዳረሻቸው የጠፉ ሰዎች መዳረሻቸው እንዲታወቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያለማቋረጥ ጥሪ አድርጓል፣ የፖለቲካ እሰረኞችንና በጨካኙ አገዛዝ ገዳዮች የተገደሉ ሰዎችን ቤተሰቦች ረድቷል፣ በታወቁና በድብቅ የአገዛዙ እስርቤቶች ውስጥ ታግተው የሚማቅቁ በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ሰቆቃ እና የመለስን አገዛዝ መረን ያጣ የሰብአዊ መብት ጥሰት አጋልጧል።

ለዚህ ጥረቱ መሳካትም እገዛ የሚያገኘው በመላው ዓለም ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የበጎ ፈቃድ ደጋፊዎቹ ነው። ስራውን የሚያካሂዱት መላው አባላቱም የሚሳተፉት በነፃ በጎ ፈቃደኛነት ነው። በሀገር ቤት ውስጥ፣ በጨካኙ የሰብአዊ መብት አፋኝ አገዛዝ ጥላ ሥር በምሥጢር ስራቸውን የሚያካሂዱት አባላቱ ያለባቸው አደጋ ቀላል አይደለም። የሚከፍሉት መስዋዕትነት ሕይወትንም የሚጠይቅበት ወቅት አለ። በምስጢር ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጉ ከነበሩት የኢፖእአኮ አባላት ውስጥ አንዱ የነበረው ጋዜጠኛ እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ተስፋዬ ታደሰ በመለሰ ዜናዊ የደህንነት ሃይሎች፣ አዲስ አበባ ውስጥ ታርዶ ተገድሏል። ስለዚህም ተስፋዬንና ሌሎችንም ለሰብአዊ መብት መከበር ሲታገሉ የወደቁ ጀግና አባላቱን በኩራት ያስባቸዋል።

ኢፖእአኮ በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በኖርዌይና በሌሎችም ቦታዎች በሚገኙ ስደተኞች ላይ የሚደርሰውን መንገላታትና ለሚያቀርቡት የፖለቲካ ጥገኝነት ከለላ ጥያቄ የሚሰጣቸውን የእምቢታ መልስ በመኮነን ድምፁን አሰምቷል። በምንም ሰበብም ይሁን በምንም ስደተኞች እና የፖለቲካ እስረኞች ለሚያሰሙት የሰቆቃ ድምጽ ጆሮ ዳባ ልበስ የሚሉ የውጭ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ድርጅቶችን ተችቷል። መዳረሻቸው የጠፋው የኢሕአፓ መሪዎችና አባላት፣ ከህግ አግባብ ውጭ ታስሮ የሚገኘው አበራ የማነአብ፣ ጋዜጠኛ ብርሃኑ እጅጉ፣ መዳረሻው የጠፋው የሙያ ማህበር መሪ አበበ ዓይነኩሉ እና ሌሎችም በባዕዳኑም ሆነ በሀገር ቤቶቹ የሰብአዊ አጠባበቅ ድርጅቶች ስማቸው አይነሳም። ኢፖእአኮ ግን ስማቸውን አጉልቶ አስደምጧል፣ መዳረሻቸው እንዲታወቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጠይቋል።

ኢፖእአኮ 16ኛ ዓመቱን የሚያከብረው ሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ እንዲከበሩ ለመታገል የገባውን ክቡር ቃል-ኪዳን ዳግም በማደስ ነው። ኢፖእአኮን በገንዘብም ሆነ በሌላ መንገድ መርዳታቸውን ይቀጥሉ ዘንድም ለሁሉም ደጋፊዎቹ ጥሪውን ያስተላልፋሉ።


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE